# የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን | ETHIOPIAN NATIONAL DIALOGUE COMMISSION

## ተሳታፊዎችን ለመለየት እና አጀንዳ ለማሰባሰብ የተዘጋጀ አሰራር ስርዓት

# ይዘት

1. መግቢያ
2. የተሳታፊዎች ልየታ
3. ከወረዳዎች የሚወከሉ የህብረተሰብ ክፍሎች
4. ከክልሎች የሚወከሉ የህብረተሰብ ክፍሎች
5. ከፌዴራል የሚወከሉ የህብረተሰብ ክፍሎች
6. የተሳታፊዎች የውክልና ሂደት
7. አጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት


# መግቢያ

- ኮሚሽኑ አሳታፊ፣ አካታች፣ የህብረተሰብ ባለቤትነትን ያረጋገጠና ተፈጻሚነት ያለው ሂደት ለማድረግ ተሳታፊዎችን ከወረዳዎች (ልዩ ወረዳዎች) ጀምሮ ለመለየት ወስኗል፡፡
- ባዘጋጀው የአሰራር ስርዓቶች ላይ የወረዳና የዞን አስተዳዳሪዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ሲቪክ ማህበራትና ፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች ጋር ውይይቶችን አካሂዶ ግብዓቶችን ሰብስቧል፡፡

# 1. የምክክር ሂደት ተሳታፊዎችን መለየት

ኮሚሽኑ አራት የትኩረት ቦታዎች፡-

1. ክልሎች
2. ከተማ መስተዳደሮች
3. በፌደራል ደረጃ
4. በዲያስፖራ



# ማብራሪያ

- **በክልሎች**
  - ✓ከወረዳዎች - የህብረተሰብ ክፍል ተወካዮች ይመረጣሉ፡፡ እነዚህም ዘጠኝ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው (ዝርዝሩ በቀጣይ ስላይዶች ላይ ይገኛል)፡፡
  - ✓ከክልል ደረጃ - በተቋም የተደራጁ አካላት ናቸው፡፡ አስራ ስድስት አካላት ተወካዮቻቸውን ይልካሉ (ዝርዝሩ በቀጣይ ስላይዶች ላይ ይገኛል) ፡፡
- **በከተማ መስተዳደሮች**
  - ✓ ከወረዳዎች - የህብረተሰብ ክፍል ተወካዮች ይመረጣሉ፡፡ እነዚህም ዘጠኝ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው (ዝርዝሩ በቀጣይ ስላይዶች ላይ ይገኛል)፡፡
  - ✓በከ/መስተዳደር ደረጃ ያሉ - በተቋም የተደራጁ አካላት ናቸው፡፡ አስራ ስድስት አካላት ተወካዮቻቸውን ይልካሉ (ዝርዝሩ በቀጣይ ስላይዶች ላይ ይገኛል)፡፡

# …ማብራሪያ

- **በፌዴራል**
  - ✓በተቋም የተደራጁ አካላት ናቸው፡፡ አስራ ስምንት አካላት ተወካዮቻቸውን ይልካሉ (ዝርዝሩ በቀጣይ ስላይዶች ላይ ይገኛል)፡፡
- **በዳያስፖራ**
  - ✓በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ተወካዮቻቸውን ይልካሉ (ዝርዝሩ በቀጣይ ስላይዶች ላይ ይገኛል)፡፡

# ከወረዳዎች የሚወከሉ የህብረተሰብ ክፍሎች

- እራሳቸውን የሚገልጡበት ዋና መተዳደሪያ (livelihood)
- ሴቶች፣
- ወጣቶች፣
- ዕድሮች፣
- የማህበረሰብ መሪዎች/አባቶች/እናቶች፣
- የመንግስት ሰራተኞች፣
- መምህራን ፣
- (marginalized) - ባለሙያዎች ፣
- የንግድ ማህበረሰብ

# በክልል ደረጃ የሚወከሉ ባለድርሻ አካላት –1

- ሲቪል ማህበራት (በክልል የተመዘገቡ)፣
- የክልል የጋዜጠኞች ማህበር/ የሚዲያ ተቋማት ማህበር፣
- የቀድሞ ሠራዊት ማህበር/ የተቀናሽ ሠራዊት ማህበር፣
- የክልል መንግስት ካቢኔ፣
- የክልል ምክር ቤት፣
- የክልል ፍርድ ቤቶች፣
- የክልል ፖሊስ፣
- ታዋቂ ሰዎች፣

# በክልል ደረጃ የሚወከሉ ባለድርሻ አካላት –2

- የአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣
- የሃይማኖት ተቋማት፣
- የሰራተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን፣
- የአሰሪዎች ማህበራት
- የፖለቲካ ፓርቲዎች
- የንግድ ምክር ቤት/ ዘርፍ
- የመምህራን ማህበር
- እንደየክልሉ ሁኔታ የሚታከሉ ናቸው

# በፌዴራል ደረጃ የሚካተቱ ተሳታፊዎች – 1

- የፌደራል መንግስት
- የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
- የፌዴሬሽን ምክር ቤት
- የፌዴራል ፍርድ ቤት
- ሀገር አቀፍ ፖለቲካ ፓርቲዎች
- የመከላከያ ሰራዊት
- የፌደራል ፖሊስ
- የአሰሪዎች ፌዴሬሽን
- የሰራተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን

# በፌዴራል ደረጃ የሚካተቱ ተሳታፊዎች – 2

- የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር
- ዩንቨርሲቲ መምህራን
- የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን
- የአረጋዊያን ማህበራት ፌዴሬሽን
- የሴቶች ጥምረት ለምክክር
- የፌዴራል ንግድ ምክር ቤት
- ታዋቂ ሰዎች
- የሃይማኖት ተቋማት

# በፌዴራል ደረጃ የሚካተቱ ተሳታፊዎች – 3

- ማህበራዊ አንቂዎች እና ተጽዕኖ ፈጣሪዎች
- በፌዴራል ደረጃ ያሉ ሲቪል ማህበራት

✓ የሰብዓዊ መብት ተቆርቃሪዎች
✓ በልማት የተሰማሩ
✓ በዲሞክራሲ ላይ የሚሰሩ
✓ የጤና ባለሙያዎች ማህበር
✓ የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት
✓ የጠበቆች ማህበር
✓ የሙያ ማህበራት
✓ የስነ ጥበብ ባለሙያዎች ማህበራት....

# ከዳያስፖራ የሚወከሉ ተሳታፊዎች

- ከአምስት ዋና ዋና የዓለማችን ክፍሎች የሚወከሉ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ይኖራሉ።

እነዚህም፡-

1. አሜሪካና ካናዳ
2. አውሮፓ
3. እስያና ኦሺኒያ
4. አፍሪካ
5. መካከለኛው ምስራቅ ናቸው።

# የተሳታፊዎች ቁጥር

- ኮሚሽኑ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ባለድርሻ አካላት፣ ከመንግስት፣ ከሃሳብና ፖለቲካ መሪዎች የሚወከሉትን ተወካዮች ለመወሰን በርካታ የፖሊሲ ሃሳቦችን ተመልክቶ መነሻ የሚሆኑ ቁጥሮችን አስቀምጧል (2000)፡፡
- በክልሎችና ከተማ መስተዳደሮች እንዲሁም በፌዴራል የሚካሄዱ የአጀንዳ ማሰባሰቢያ ውይይቶች የተለያየ ቁጥር ቢኖራቸውም ትልቁ 2000 ተሳታፊዎች እንዲሆን ኮሚሽኑ ወስኗል፡፡
- ይህንን መነሻ በማድረግ ኮሚሽኑ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የተሳታፊዎችን ቁጥር አስቀምጧል፡፡

# የተሳታፊዎች ቁጥር የፖሊሲ ውሳኔ መነሻ የሆኑት የሚከተሉት ምክንያቶች ናቸው፡-

- የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት በእያንዳንዱ ክልል ለየብቻ የሚካሄድ ሂደት ስለሆነ የአንድ ክልል የተሳታፊዎች ቁጥር በሌላው ክልል ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ የሌለው በመሆኑ፣
- ከተለያዩ ወረዳዎች ተወክለው የመጡ የህብረተሰብ ክፍሎች በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ውስጥ እምነት የሚጣልበት (credible) ድምጽ ማሰማት በሚችሉት ብዛት መሰባሰባቸው ለሂደቱ ቅቡልነት አስፈላጊ በመሆኑ፣

# የፖሊሲ ውሳኔ መነሻ የሆኑት የሚከተሉት ምክንያቶች ናቸው፡-

- በተቻለ መጠን የሚዘጋጁት መድረኮች ለማወያየትና ሃሳቦችን በተገቢው መንገድ ለመስጠት ምቹ እንዲሆን ለማስቻል፣
- በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት የሚቀርቡ አጀንዳዎች በሙሉ ተጠናቅረው ወደ ኮሚሽኑ ምክር ቤት የሚመጡ ሲሆን የመድረኮቹ ተሳታፊዎች ቁጥር በሚሰበሰቡት አጀንዳዎች ላይ ተጽዕኖ የማያሳድሩ መሆኑ፣
- የኮሚሽኑ አጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ላይ የሚቀርቡ አጀንዳዎች ላይ በድምጽ ብልጫ የሚወሰኑ ውሳኔዎች የሌሉ መሆናቸው ናቸው፡፡

# በክልሎች ደረጃ የሚለዩ ተሳታፊዎች ብዛት ማብራሪያ

- **የክልል መንግስት (አስፈጻሚ)፡-** እንደክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የሚወሰን ቢሆንም በ50 ሰዎች ይወከላል፡፡
- **የክልል ምክር ቤት፡-** የክልሉ ምክር ቤት ጠቅላላ አባላት ብዛት ከ200 በታች ከሆነ በ30 ሰዎች፣ ከ200-400 ከሆነ በ50 ሰዎች እንዲሁም ከ400 በላይ ከሆነ በ70 ሰዎች ይወከላሉ፡፡
- **የክልል ፍ/ቤቶች፡-** በሁሉም ደረጃ ያሉ ፍርድ ቤቶች በ30 ሰዎች ይወከላሉ፡፡
- **የአካል ጉዳተኞች ማህበራት፡-** የክልል የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ያሉት የጉዳት ዓይነቶችን በማካተት ከእያንዳንዱ ሁለት ተወካዮች ይኖራሉ፡፡

# በክልሎች ደረጃ የሚለዩ ተሳታፊዎች ብዛት ማብራሪያ

- **ታዋቂ ሰዎች፡-** እንደአከባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በአብዛኞቹ ክልሎች 20 በኦሮሚያ፣ አማራና አዲስ አበባ እስከ 100 ሰዎች ይለያሉ፡፡
- **የሃይማኖት ተቋማት፡-** ቀደም ተብሎ በተዘረዘረው ማብራሪያ መሠረት ከእያንዳንዱ ሃይማኖት 3 ተወካዮች ይለያሉ፡፡
- **የፖለቲካ ፓርቲዎች፡-** በክልሉ ውስጥ ያሉ ፖለቲካ ፓርቲዎች አምስት አምስት ተወካዮችን ይልካሉ፡፡ ይህ የተደረገው በአብዛኛው የፖለቲካ አመራሮች በ5 የተዋቀሩ በመሆናቸው ያንን ከግምት በማስገባት ነው፡፡

# በፌዴራል የሚገኙ ተሳታፊዎች ብዛት

| ቁጥር | ባለድርሻ አካላት | የተወካዮች ብዛት |
|---|---|---|
| 1. | የፌደራል መንግስት (አስፈጻሚ) | 50 |
| 2. | የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት | 50 |
| 3. | የፌዴሬሽን ምክር ቤት | 28 |
| 4. | የፌዴራል ፍርድ ቤት | 10 |
| 5. | ሀገር አቀፍ ፖለቲካ ፓርቲዎች | 44 |
| 6. | የመከላከያ ሰራዊት | 50 |
| 7. | የፌደራል ፖሊስ | 30 |
| 8. | የአሰሪዎች ፌዴሬሽን | 10 |
| 9. | የሰራተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን | 20 |
| 10. | የመምህራን ማህበራት ፌዴሬሽን | 20 |
| 11. | ዩንቨርሲቲ መምህራን | 30 |
| 12. | የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን | 10 |
| 13. | የአረጋዊያን ማህበራት ፌዴሬሽን | 10 |
| 14. | የሴቶች ጥምረት ለምክክር | 30 |
| 15. | የፌዴራል ንግድ ምክር ቤት | 10 |
| 16. | ታዋቂ ሰዎች | 50 |
| 17. | ማህበራዊ አንቂዎች እና ተጽዕኖ ፈጣሪዎች | 20 |
| 18. | በፌዴራል ደረጃ ያሉ ሲቪል ማህበራት | 50 |
| | **ጠቅላላ** | **522** |

# ማሳሰቢያ

- ከላይ የተዘረዘሩት ቁጥሮች እንደየአከባቢው ሁኔታ ወይም ከባለድርሻ አካሉ ከሚገኝ መረጃ መሠረት በማድረግ የሚስተካከሉ ይሆናሉ፡፡

# የተሳታፊዎች ውክልና ሂደት

የተሳታፊዎች ውክልና ሂደት በተለያዩ ቦታዎች የተለያየ ነው፡፡

እነዚህም፡-

1. በወረዳዎች በተባባሪ አካላት አማካኝነት

2. በክልል፣ ከተማ መስተዳደር እና በፌዴራል በደብዳቤ

3. ዳያስፖራ በኮሚቴዎች

# በወረዳ የሚወከሉ ተሳታፊዎች የልየታ ሂደት

1
- ተባባሪ አካላትን መለየትና ደብዳቤ መጻፍ

2
- ከተባባሪ አካላት ጋር ውይይትና ግንዛቤ ማስጨበጥ

3
- ተሳታፊዎችን መለየት

# ተባባሪ አካላት

- የወረዳ አስተዳደር ተወካይ
- ዕድሮች
- የሃይማኖት መሪዎች
- ዳኛ
- ሲቪክ ማህበራት
- የፖለቲካ ፓርቲዎች
- የመምህራን ማህበር

# ተባባሪ አካላት ተግባራትና ኃላፊነቶች

- ተባባሪ አካላት ከየወረዳው ይመለመላሉ፡፡
- ከየወረዳው የሚወጡ ተባባሪ አካላት በኮሚሽኑ በሚዘጋጁ ስልጠናዎች ላይ በመሳተፍ ስለሂደቱ መረዳት ፡፡
- ተባባሪ አካላቶቹ ከስልጠናና ውይይቶች በመቀጠል በደብዳቤ የሚጠሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ደብዳቤ አድርሰው፣ ተሳታፊዎች መወከላቸውን ይከታተላሉ፡፡
- በደብዳቤ መጠራት የማይችሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ሊወክሉ የሚችሉ ግለሰቦችን ለመለየት ተወያይተው የጋራ ስምምነት በማድረግ የስም ዝርዝር ያዘጋጃሉ፡፡ እንደአስፈላጊነቱ የተለያዩ ሌሎች አካላትን ድጋፍ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

# የተባባሪ አካላት ተግባራትና ኃላፊነቶች

- የተወካዮች መረጣ ሂደት ስብሰባዎችን በማካሄድ ተወካዮች እንዲመረጡ ያመቻቻሉ።
- ተሳታፊ የሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን አንድ ላይ በመሰብሰብ ስለምክክር፣ በውክልና ስለመሳተፍ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ይካሄዳሉ።
- የተወካዮች መረጣ በየህብረተሰብ ክፍሎች እንዲያካሂዱ ያመቻቻሉ። ይህ ሂደት ነጻ፣ አሳታፊ እንዲሆን ያመቻቻሉ
- ከውክልና ሂደቶቹን ተከትሎ አስፈላጊ ሰነዶች አዘጋጅተው ለኮሚሽኑ ይልካሉ።

# የህብረተሰብ ክፍሎች አጠራር ሂደት

- በወረዳ ደረጃ የተለዩት የህብረተሰብ ክፍሎች እያንዳንዳቸው ሃምሳ ሰዎችን በማሳተፍ ተወያይተው ተወካዮቻቸውን ይመርጣሉ፡፡
- በየህብረተሰብ ክፍሎች የሚጠሩት 50 ሰዎች በሁለት ዋና መንገዶች ጥሪው ይደርሳቸዋል፡፡

1. በማህበራት የተደራጁ ከሆኑ በኮሚሽኑ በተላከ የጥሪ ደብዳቤ በቀጥታ ተወካይ እንዲልኩ ይጠየቃሉ፡፡ ደብዳቤዎቹ በወረዳ ለሚገኙት አደረጃጀቶችና ከፍተኛው አደረጃጀታቸው ይላካል፡፡
2. አደረጃጀት ለሌላቸው አካላት ደግሞ አጋዥ አካላት ተስማምተው የሚለዩዋቸው ግለሰቦች ይሆናሉ

# የአጠራር ሂደት

1. **እራሳቸውን የሚገልጡበት ዋና መተዳደሪያ ያላቸው** (livelihood)

- በየአከባቢው ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል
- አርሶ አደር - ሁለገብ አርሶ አደር - ከፊል አርሶ አደር
- አርብቶ አደር - ከፊል አርብቶ አደሮች
- የማዕድን አውጪዎች - አንጥረኞች እና ብረታ ብረት ስራ ላይ የተሰማሩ (ወርቅ፣ድንጋይ ከሰል) (ባሉበት አከባቢ)
- የአሳ አጥማጆች (ባሉበት አከባቢ)

ማህበር ካላቸው ለማህበር ደብዳቤ በመላክ ነገር ግን በማህበር ያልታቀፉን ግን ለማካተት ጥረት መደረግ አለበት

# ...የአጠራር ሂደት

**2. እድሮች**

- እድርና የእድሮች ጥምረት
- **በአከባቢው ለሚገኙ እድሮች ደብዳቤ ይጻፋል።**

**3. ሴቶች**

- የሴቶች ሊግ - በደብዳቤ
- የሴቶች ፌዴሬሽን - በደብዳቤ
- የሴቶች ማህበር - በደብዳቤ
- የነጋዴ ሴቶች/ Informal sectors (መንግስት ያልመዘገባቸው አደረጃጀት ውስጥ ያሉ) ሴቶች - የተወሰኑትን በማህበር ሌሎቹን በተመረጡት ተባባሪ አካላት

# ...የአጠራር ሂደት

## 4. ወጣቶች

- የወጣቶች ፌዴሬሽን - በደብዳቤ
- የወጣቶች ማህበር - በደብዳቤ
- የወጣቶች ሊግ - በደብዳቤ
- በሃይማኖት ድርጅት ስር የተደራጁ ወጣቶች - በተለዩት አጋዥ አካላት ምክር መሠረት
- መንግስት ያልመዘገባቸው አደረጃጀት ውስጥ ያሉ (informal sector) - በተለዩት ተባባሪ አካላት ምክር መሠረት

# ...የአጠራር ሂደት

## 5.የማህበረሰብ መሪዎች/አባቶች/እናቶች

- በአከባቢው የሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎች፣ እናቶችና የሀሳብ መሪዎች
- የአረጋውያን ማህበር
- የገዳ ስርዓት አስተዳደር ማህበር (ኦሮሚያ)
- ሀደ ስቄ
- የአባት አርበኞች
- የጎሳ መሪዎች / አባገዳዎች
- የጎሳ ሽንጎ መሪዎች (ጉራጌ ዞን)፣ ባህላዊ መሪዎች
- ✓ በተለዩት ተባባሪ አካላት ምክር መሠረት

# ...የአጠራር ሂደት

**6. መምህራን**

- የመምህራን ማህበር
- የቀድሞ መምህራን
  - በደብዳቤ ይጠራሉ

**7. የመንግስት ሰራተኞች**

- የሴክተር መስሪያ ቤቶች ሰራተኞች፣ የወረዳ አስተዳዳሪዎች፣ ፖሊሶች
  - በደብዳቤ ይጠራሉ

# ...የአጠራር ሂደት

## 8. የንግድ ማህበረሰብ

- የሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበራት - በደብዳቤ
- የንግድ ማህበረሰብ ንግድ ምክር ቤት - በደብዳቤ
- የሆቴል ማህበር - በደብዳቤ
- የኢንቨስተሮች ፎረም - በደብዳቤ
- የእደጥበብ ባለሙያዎች - በደብዳቤ
- የህዝብ ማመላለሻ ማህበር (ኦሮሚያ) - በደብዳቤ
- የታክሲዎች ማህበር (ባጃጅ)- በደብዳቤ
- የህብረት ሥራ ማህበራት - በደብዳቤ
- የጉሊት ገበያ የሚሰሩ ማህበራት (ቤኒሻንጉል)- በደብዳቤ
- የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች - በደብዳቤ
- ሌሎች በማህበራት ያልታቀፉ ካሉ በተለዩት ተባባሪ አካላት ምክር መሠረት

# …የአጠራር ሂደት

## 9. የእጅ ባለሙያዎች (ግፉዓን) (marginalized)

- በአከባቢው ድምጻቸው የማይሰማ ክፍሎች የአከባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የሚያካትት መሆን አለበት፡፡
- በተለዩት ተባባሪ አካላት ምክር መሠረት

# 2. በክልል ደረጃ የሚደረግ አጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት

- ከወረዳዎች የተለዩት ተሳታፊዎች አንድ ላይ በመሰባሰብ በየህብረተሰብ ክፍሎቻቸው ለምሳሌ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የንግድ ማህበረሰብ፤ በመሆን የክህሎት ስልጠና ይወስዳሉ፣ አጀንዳዎቻቸው ላይ ውይይት ያደርጋሉ፡፡
- የተወሰኑት ክልሎች አጀንዳዎቻቸውን ወደ ክልል ይዘውላቸው የሚሄዱ ተጨማሪ ተሳታፊዎችን ይወክላሉ፡፡
- በክልል ደረጃ የተለዩ ተሳታፊዎች በራሳቸው አጀንዳዎቻቸውን ይሰበስባሉ

# አጀንዳ ማሰባሰብ

- በክልሎችና ከተማ መስተዳደሮች ደረጃ አጀንዳዎች በሕዝባዊ ውይይቶች ይሰበሰባሉ፡፡
- ውይይቶቹ በጋራና በቡድን የሚደረጉ ይሆናሉ፡፡



# አጀንዳ ቀረጻ

- አጀንዳዎች በየጭብጣቸው ከተጠናቀሩ በኋላ በኮሚሽኑ ምክር ቤት ይቀረጻሉ፡፡
- ከተሰበሰቡት አጀንዳዎች እጅግ መሠረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች የሆኑት የሀገራዊ ምክክር አጀንዳ ሆነው ይቀረጻሉ፡፡
- የተቀረጹት የሀገራዊ ምክክር አጀንዳዎች ለህዝብ ይፋ ይሆናሉ፡፡